# *ለዘመናት በፍቅርና መከባበር የኖረን ህዝብ በደረቅ ፕሮፖጋንዳ መነጣጠልና መከፋፈልም ሆነ የመብት ጥያቄውን ማዳፈን አይቻልም!!*

***በጂሃድ ሃረካት ፊልም ላይ ከ 33ቱ ፔቲሺን ፈራሚዎች የተሰጠ መግለጫ***

*ንብረትነቱ የህዝብ ቢሆንም አገልግሎቱ የኢህአዴግ የፕሮፖጋንዳ መሣሪያ የሆነው ኢቲቪ በሰሞኑ የፍርድ ቤት እግድ ወደጎን በመግፋት ከተለያዩ ፊልሞች በመቀነጫጨብ "ጂሃዳዊ ሃረካት " በማለት ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ባለው በእሥር ላይ የሚገኙት የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ላይ ያነጣጠረ ፊልም በተደጋጋሚ አሰራጭቶ ተከታትለናል።*

*የፊልሙ ዓላማ የህዝብን የዘመናት አብሮነት መሸርሸርና የመብት ጥያቄ የሚያነሳን ከሽብርተኝነትና ጦርነት ጋር በማያያዝ ህዝብን ለማሸማቀቅ ሆኖ በውጤቱም ህዝብ በአገሩ ላይ ያለውን የባለቤትነትና ኃላፊነት ስሜት በመናድ አንገት ማስደፋትና መብት ጠያቂዎችን በመነጣጠልና መከፋፈል ጥያቄዎችን ማዳፈንና ማፈን ነው፡፡ ኢህአዴግ በለመደው መንገድ ፊልሙን ሲያዘጋጅ በኮሚቴ አባላት ላይ ለከፈተው የፈጠራ ክስ በፍትህ አደባባይ ሊያቀርብ ያልቻለውን መረጃና ማስረጃ በህገ ወጥ መንገድ ታሳሪዎችን በማሰቃየት "ከተናገሩት"ና (ቅንብሩ ሣይጠናቀቅ አምልጦ በተላለፈው ፊልም እንደተረጋገጠው) ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ጉዞው ከተለያዩ ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅ ካልሆኑ የሌላ አገር ፊልሞችን ጨምሮ በተቀናበረ የፕሮፖጋንዳ ድርሰት ለማስደገፍ ቢሆንም የተፈለገውን ውጤት አላስገኘለትም። ይልቁንም በተደጋጋሚ ስንገልጽ የነበረውን ኢህገመንግሥታዊና ከህግ የበላይ ነኝ በሚል የገፋበትን የማንአለብኝነት ባህሪይውን ፍንትው አድርጎ አሳይቷል፡፡*

*መንግሥት ትናንት የኮሚቴ አባላቱን ውክልና ተቀብሎ ሲያወያይ እንዳልነበረ ውይይቱ ያለውጤት ሲቋረጥ "አሸባሪ " በሚል መክሰስ የሚያሳየው ኢህአዴግ በባሕሪይው የተለየ ኃሳብና ጥያቄ ካላቸው ወገኖች ጋር ተወያይቶ መፍትኄ ለማምጣት ድፍረትና የሞራል መሠረት የሌለው፤ህግን ለሀገርና ህዝብ ደህንነት መጠበቂያ*

ሣይሆን ለራሱ ለፓርቲው ጠባብ ፍላጎትና ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲሁም የማይመቹትን ያላግባብ ለመጉዳት የሚጠቀም መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መንገድ የኮሚቴ አባላቱን ወህኒ ከወረወረ በኋላ ፡

1ኛ/ የህግ የበላይነት ምሰሶ የሆነውን '' የተጠርጣሪዎችን ከፍርድ ቤት ውሳኔ በፊት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት (Presumption of Innocence) '' በመጣስ፤

2ኛ / በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 19(5) የተጠቀሰውን « የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡» የሚለውን በመጣስ፤

3ኛ/ተጠርጣሪዎች በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 (3) ላይ የተሰጣቸውን '' በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምሥክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ መብት'' በመግፈፍ፤

4ኛ/ ተጠርጣሪዎች በፍትህ አደባባይ ''ወንጀል ተፈፀመብን እንጂ ወንጀል አልፈፀምንም ''ሲሉ የሰጡትን ቃል ለመሸፈን ይህን ህገወጥ ፊልም ማዘጋጀቱና ማሠራጨቱ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው፡፡

ከዚህም የሥርዓቱ ህልውና በሰለጠነ መንገድ ከመወያየት ይልቅ በማጭበርበር፣ ህዝብ ከህዝብ በማጋጨትና በመነጣጠል፣ በማሸበርና በሀሰት ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ በአደባባይ ለመከራከርና መፍትሄ ለመሻት ተፈጥሮውና ባህሪይው እንደማይፈቅድለት እንረዳለን፡፡

ይህ ህዝብን ከመናቅ የመነጨ ''ተጨፈኑ ላሞኛችሁ'' በሚል በተደጋጋሚ የተላለፈ ድራማዊ ፊልም ትናንት በቅንጅት፣ በቅርቡ ደግሞ ''አኬልዳማ'' በሚል በእነ እስክንድር ነጋ ላይ የተዘጋጁ ፊልሞች ጋር ተመሣሣይ ዓላማ ያለው በመሆኑ ህዝብ ከመለቀቁ አስቀድሞ ውሸት መሆኑን ደምድሟል። በተጨማሪም ፊልሙ ኢ.ህአዴግ ለ21 ዓመታት ልዩነትን በማራገብ ህዝቡን በጎሣ፣በብሄር፣በክልል ፣በሃይማኖት...ለመከፋፈል፣ለመነጣጣል፣ለማጋጨት...ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት ቀጣይ መሆኑን ህዝቡ ተረድቶታል።በመሆኑም ይህ የዘመኑን የዕድገት ደረጃ የትውልዱን የመረጃ ትንተና ችሎታና የማገናዘብ ደረጃ የማይመጥን ፊልም አንዳች

የፕሮፖጋንዳ ጥቅም ያለማስገኘቱን፣ የኮሚቴ አባላቱን ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ያለመነጠሉን፣ ከዓመት በላይ የመንግሥትን ትንኮሳ በመከላከል ጭምር የተካሄደው ተከታታይ የሙስሊሞች የእምነት መብት ጥያቄና ለኮሚቴው ያላቸው ድጋፍ ተጠናክሮ ሲቀጥል ተመልክተናል። በህዝበ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ መካከልም የመከፋፈልና የጥርጣሬ ስሜት ከመፍጠር በተቃራኒው ኅብረተሰቡ እንዲተባበርና በጋራ እንዲቆም ትምህርት ሰጥቷል። በጥቅሉ በዚህ ፊልም የተሞከረው የተለመደው የኢህአዴግ ህዝብን ከህዝብ በማጋጨት "ያለእኔ አደጋ ውስጥ ናችሁ"በሚል ፕሮፖጋንዳ ራሱን ገላጋይ በማድረግ ሥልጣን የማራዘም ስልት ላይ ተመርኩዞ የተደረገው ጥረት መክሿል፡፡

የዚህ ፊልም ከዝግጅቱ እስከ ውጤቱ ያለው ሂደት ገሃድ ያደረገውና የበለጠ ያረጋገጠው ሲጠቃለል፡

ሀ/ የሙስሊሙ ኮሚቴዎች ሽብርተኛ መሆናቸውን ሣይሆን ገዢው ፓርቲና መንግሥት ራሣቸው ያወጡትን ህገ መንግሥትም የማያከብሩና ከህግ በላይ መሆናቸው፤

ለ/ የሙስሊሙ ኮሚቴዎችን ከህዝበ ሙስሊሙ መነጠልም ሆነ ድጋፍ ማሳጣትእንዲሁም ሠላማዊ ተቃውሞውን ሊቀለብሰው ቀርቶ ሊያበርደው ያለመቻሉን፣ ብቻ ሣይሆን የህዝቡ በኮሚቴ አባላት ላይ ያለው እምነት መጠናከሩን፤ በሙስሊሙና ክርስቲያኑ ህዝብ መካከል ባለው የዘመናት መከባበርና አብሮነት ቀጣይነት ላይ ችግር ያለመፈጠሩ፤

ሐ/ ገዢው ፓርቲ/ መንግሥት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ረግጠው ፊልሙን ማስተላለፋቸው ህዝቡ የህግ ከለላና ዋስትና የሌለው መሆኑን ፣አገሪቱን የሚያስተዳድረው መንግሥት ለህግ ተገዢነቱ አሳሳቢና አጠያያቂ ደረጃ ላይ መድረሱን፤

መ/ ገዢው ፓርቲ/ መንግሥት ለህዝብ ያላቸው ንቀትና ማንአለብኝነት ገደቡን ያለፈ ብቻ ሣይሆን የፍርድ ቤቶች ህገመንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት በአስፈጻሚው መነጠቁን፣የህግ ባለሙያዎችን ተቀባይነት አጠያያቂ የሚያደርግና አንገታቸውን የሚያስደፋ መሆኑ፤

ሠ/ የፊልሙ ህዝቡን በመለያየት፣ በመከፋፈል፣ በማሸማቀቅ ...የመብት ጥያቄዎችን የማዳፈንና ማፈን ዓላማ ያለመሳካቱ ብቻ ሣይሆን ህዝቡ ከመቼውም ጊዜ በላይ በመንግሥት ላይ ያለው እምነት እንዲሟጠጥ፣የለውጥ ፍላጎቱ እንዲጨምርና ለመብቱ በጋራ እንዲነሳ ያደረገው መሆኑ፤ ናቸው።

በመሆኑም ገዢው ፓርቲ/ መንግሥት የመብት ጥያቄ ያነሳን ወገን ህገ መንግሥታዊ መብት በመጨፍለቅ በፈጠራ ወንጀል"አሸባሪ" "ጦረኛ "በማለት መወንጀል ፣ከፍርድ ቤት ውሳኔ በፊት በህዝብ ሃብት በሚተዳደር መገናኛ ብዙሃን ወንጀለኛ አድርጎ ማቅረብ፣የፍርድ ቤት ውሳኔን መጣስ፣ በአጠቃላይ በፊልሙ ዙሪያ የተፈፀመው የማይታለፍ ወንጀል ስለሆነ፡

1ኛ/ገዢው ፓርቲ/ መንግሥት ከዚህ ዓይነቱ ተግባር እንዲቆጠብ፤ እንዲሁም-

- የተጠርጣሪዎችን መብት በመርገጥ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ራሣቸውን መከላከል በማይችሉበት ታስረው ባሉበት "ዶክሜንተሪ " በሚል ክብርና ዝናቸውን የሚያጎድፍ፣ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ፊልም አዘጋጅቶ፤
- በህዝብ ሃብት የሚተዳደረው ኢቲቪ የተጠርጣሪዎችን መብት ከመድፈር በተጨማሪ ነጻ ኃሳባቸው ያልተካተተበትን ፊልም ማስተላለፍ ብቻ ሣይሆን የፍርድ ቤት የእግድ ውሳኔ በመጋፋት ያስተላለፈ/ያሰራጨ በመሆኑ፤
- አስፈጻሚው የዜጎችን ህገ መንግሥታዊ መብት የማክበር፣የህግ የበላይነትን የማክበርና ማስከበር፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ፤ በህግ እንዲጠየቁ በማድረግ ለህገ መንግሥቱ ያለውን ታማኝነት እንዲያረጋግጥ፤
- መንግሥት የሙስሊሙን መሪዎች እንዲፈታ፣ለሙስሊሙ ህዝብ ጥያቄዎች የሰከነ ምላሽ እንዲሰጥ፣ ኃይማኖታቸውን በራሳቸው የመምራት ህገ መንግሥታዊ መብት እንዲያከብር፣ ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆም፤

2ኛ/ጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት ሙስሊሙ ህዝብ ጥቂት ያለመሆኑን በማስመስከር ህገ መንግሥታዊ የእምነት ነጻነቱን ለማስከበር እያደረገ ያለውን ሠላማዊ ተከታታይ ትግል ፣ለኮሚቴ አባላት ያሳየውን ጠንካራ ድጋፍ፤ የኮሚቴ አባላቱ ለዓላማቸው ያሳዩትን ጽናት ፣ እንዲሁም ጠበቆች ሙያዊ ቃልኪዳናቸውን በማክበር ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ያሳዩትን ቁርጠኝነት በተምሳሌትነቱና ትምህርት

ሰጪነቱ እያደነቅን ፤ መላው ኢትዮጵያዊ ገዢው ፓርቲ/ መንግሥት የመረጠው አካሄድ ችግሮችንና ጥያቄዎችን በሠለጠነ መንገድ በውይይት መድረክ ከመፍታት ይልቅ ጠያቂዎችን ''ከፋፍለህ/ነጣጥለህ ምታ '' አማራጭን ስለሆነ በዝምታ በተናጠል ለመመታት ወር ተራችንን ከመጠበቅ ለዲሞክራሲና ሰብዐዊ መብት መከበር ህገ መንግሥቱ በተግባር እንዲተረጎም በሚደረገው ሠላማዊ ትግል በህብረትና ቆራጥነት በጋራ እንድንቆም፤

3ኛ/ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ ለዲሞክራሲ ሥርዓት የቆማችሁ መንግሥታት፣የሰብዐዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ተሟጋች ተቋማት...ከህዝቡ ሠላማዊ ትግል ጎን በመቆም የአምባገነን መንግሥት ሣይሆን የህዝብና የዲሞክራሲ ወገንተኝነታችሁን በተግባር እንድታረጋግጡ፤ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የተባበረና የተቀናጀ ህዝባዊ ትግል ያሸንፋል//

<u>*የካቲት 05/ 2005 ዓ.ም ፤*</u>

<u>*አዲስ አበባ*</u>

<u>*የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር*</u>

| *ሥም* | *የሥራ ኃላፊነት* | *ፊርማ* |
|---|---|---|
| *አስራት ጣሴ* | *ሰብሳቢ* | |
| *ወንድማገኘሁ ደነቀ* | *ም/ሰብሳቢ* | |
| *ግርማ በቀለ* | *ፀሃፊ* | |
| *ስለሺ ፈይሣ* | *ም/ፀሃፊ* | |
| *አለሣ መንገሻ* | *አባል* | |
| *ኤርሚፎ ኤርዴሎ* | *አባል* | |
| *ኑሪ ሙዴስር* | *አባል* | |
| *ገብሩ ገ/ማሪያም* | *አባል* | |